Title: Mahmoud Mohammed Interview

Creators: Mohammed, Mahmoud; Bekele, Getnet

Date: July 31, 2010

City: Ali Wayao

Country: Ethiopia

African Oral Narratives: aodl.org/oralnarratives

ይህ ቦታ አሊ ወዮ ይባላል

እኔ ፕሮፌሰር ጌትነት በቀለ ነኝ

አቶ ማህሙድ አህሙድ ጋር የተደረገ ጥያቄና መልስ ነው

July 31

ጥ. ሞዴል ገበሬ ነህ ተብሏል እንዴት ተሚጥክ ?

መ. ለመጀመሪያ ጊዜ ህይወቴን ለማሻሻል በሚደርገው ጥረት ወደግብርና ገብቼ ሥራ ኑሮዬን ለማሻሻል በምጥርበት ወቅት ጥሩ ገበሬ ነህ ትብዬ እረዱኝ እኔም በእርዳታው ራሴን እያሻሻልኩ ሄድኩኝ

ጥ. ስንት ዓመት የሆንህል እራስህን ችለህ ግብርና ስትሠራ ?

መ. አሁን 15 ዓመት ይሆነኛል

ጥ. መሬት እንዴት አገኘህ ?

መ. ከቤተሰብ ነው ያገኘሁት እንጂ ከቀበሌ ምንም አላገኘሁም

ጥ. አባትህ እዚህ ቅርብ አሉ የትኛው ነው የሳቸው መሬት ?

መ. የሳቸው መሬት ራቅ ይላል አነስተኛ ነው

ጥ. ይሄ ሜሬት ታዲያ የማን ነው ?

መ. እዚህ የቀበሌ ወፍጮ ቤት ነበር እሱን ስጠበቅ ነው የሰጠኝ

ጥ. ስንት ነው ታዲያ ይሄ ስፋቱ ?

መ. ያኔ ሲሰጠኝ እንኳን ትንሽ ነው አሁን 2 ጥማድ ይሆናል

ጥ. አንድ ጥማድ ስንት ነው በሄክታር ?

መ. ግማሽ ሄክታር ማለት ነው

ጥ. በዚህ 15 ዓመት ወስጥ ምንድነው በብዛት የምታመርተው በማሳህ ላይ

መ. ማሳ ላይ በቆሎ፣ ስንዴ አንዳንደም ሸንኮርት አመርታለሁ እዚህ ላይ ደግሞ የጓሮ አትክልትና ፍራፍሬ ጥራጥሬ ነው የማመርተው

ጥ. ማሳህ ስንት ሄክታር ይሆናል ?

መ. አንድ ሄክታር ይሆናል

ጥ. እዛ ቤት አለህ ማን ይጠብቅልሀል

መ. ሁሉም እኩል ስለሚዘራ ከብት ስለሚይለቀቅ ጠባቂ አያስፈልገወም

ጥ. ውተር ፖምፕ አለህ አሉ እወነት ነው ?

መ. አዎ አለኝ

ጥ. በአሁኑ ወቅት ያለው የገበሬ ችግር ምንድን ነው አንድ ሰው መጥቶ አንድ ችግርህን ልፍታልህ ቢልህ ምን ትላለህ ምንድነው የምትመርጠው ?

መ. እኔ በበኩሌ የገበሬዎች ገበሬነት ቢሰማን ጥሩ ነው የዚህ ኩሬ ሸራ ብቻ ነው ሌላው በሞኑ እራሴ ማስራትና ማግኘት እችላለሁ በግገዝም ይከብዳል አሉ አሁን የሚማጡ ድርጅቶች እርዳታ ይሰጣሉ ይባላል፡፡ የማመርተው በዚህ ኩሬ ስለሆነ ወሃው እንዳይሰምጥ ሸራ እፈልጋለሁ ችግሬ ይሄ ነው፡፡

ጥ. ማዳበሪያ ትጠቀማለህ ?

መ. እዚህ ግቢ ወስጥ አልጠቀምም በኮምፖስ ነው የምጠቀመው ማሳ ላይ ግን እጠቀማለሁ

ጥ. የማዳበሪያ ዋጋ እንዴት ነው ከአቅም በላይ ነው ወይስ ይቻላል ?

መ. የማዳበሪያ ጉዳይ ብዙ ወጣ ወረድ አለው በእህሉ ዋጋ ደረጃ ስታየው ወድነው ባይባልም ግን ዋጋው ከፍ ዝቅ እያለ ገበሬው የሚዘበዝበት ሁኔታ አለ ገበሬው ለሽያጭ በሚያቀርብበት ጊዜ ነጋዴው ዝቅ ያደርግና ገበሬወም ዕዳወን ለመክፈል ሸጦ ይከስራ፡፡ ግን በገበሬ አያያዝ አቆይቶ መሸጥ ስለሚይችል ከሰራ ይገባል ከዚህ ሁኔታ ሲታይ እንጂ ወድነው አይባልም ገበሬው በወቅቱ ማስቀመጥ ስለሚይችል ነው፡፡

ጥ. ከዚህ ከኩሬ ጋር ተያይዞ የወባ ስጋት አለ ምክንያቱም ትንኞች እንደዚህ ዓይነት ወሃ ካገኙ በቀላሉ ይራባሉ ይህ እንዳይሆን ማምድነው የምታደርገው

መ. እኔ በግሌ የምጠቀመው ለዚህ ኩሬ ስጋት ስላለኝ ከብትም እዚህጋ ስለሚያድር በሳምንት አንድ ጊዜ መድሀኒት እረጫለሁ ሜታ ሜታ ፋኖስ አበራና በብዛት እሱ ላይ ሲሰበሰቡ መድሀኒት እረጫለሁ፡፡ አንዳንደም ሳምንትም ላልቆይ እችላለሁ እስካሁን ያጋጠመኝ ችግር የለም

ጥ. ማለታይን ነው የምትረጨው ?

መ. አይ እኔ በግሌ ነው የግል ተሞክሮ ነው መንግስት የወባ መከላከያ አጎበር ይሰጣል ዲዲቲም ይረጫል፡፡ አንዳንድ አካባቢዎች በጣም የጎላ የወባ ችግር አለ እዚህም አካባቢ በፊት ነበር አሁን ግን አቅሟ ደከሟል የለም ነው የሚባለው፡፡

አመሰግናለሁ፡፡